የፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

# የጅምላ ትምህርት ቤት ማግኔት (A Whole School Magnet)

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች

ዓለም አቀፍ የስነ-ምህዳር (Global Ecology) ጥናቶች

ስነ-ሰው (Humanities)

ራሱን የቻለ ትምህርት/ጥናቶች

ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ የኮምፒውተር ሳይንስ




አድራሻ፡- 17501 West Willard Road
Poolesville ፣ MD 20837
ስልክ፡- 240-740-2419


ማመልከቻዎች እዚህ ይገኛሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms


MCPS
Rockville, Maryland

## እንኳን ወደ ፑልስቪል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በደህና መጡ!

## የጅምላ ትምህርት ቤት ማግኔትን ስለማስተዋወቅ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (Montgomery County Public Schools) ከፍተኛ ተነሳሽነት እና ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ፣ ጥብቅ የትምህርት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የሃያ አምስት አመት ስኬታማ ልምድ አለው። የፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለአለፉት ሰባት አመታት በዋሽንግተን ፖስት የቻለንጅ ማውጫ/ኢንዴክስ በሜሪላንድ ስቴት አንደኝነት ያገኘ (ቁጥር አንድ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደሆነ እውቅና ተሰጥቶታል። በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ፕሮግራሞች ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት ፈተና ለወሰዱ ከላይኛው ካውንቲ ስፍራዎች ለሚመጡ ተማሪዎች እንደዚሁም በፑልስቪል የመማሪያ አካባቢ ለሚኖሩ ተማሪዎች ክፍት ናቸው። የጅምላ ትምህርት ቤት ማግኔት ከፍተኛ/ልዩ ችሎታ ባላቸው መምህራን ስለሚሰጡ ለሁሉም ጥብቅ አሳታፊ ኮርሶች እድል/በር ይከፍታል። የጅምላ ትምህርት ቤት ማግኔት የተደራጀው በተረጋገጡ የማግኔት የጥናት መስኮች ላይ ትኩረት ከአደረጉ ከበርካታ ዘርፎች በተገኙ ጥቂት የአስተማሪዎች ቡድኖች በተወጣጡ የመማሪያ "ቤቶች" ("houses") ዙሪያ ነው። የሙሉ በሙሉ ትምህርት ሞዴል (The whole school model) በማመልከቻ ውድድር ሂደት የተመረጡ ተማሪዎችን፣ እንዲሁም በማግኔት የትኩረት ዙሪያዎች ፍላጎት ያላቸው የአካባቢ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ያሳትፋል እንዲሁም ያፋልማል።

ማግኔት የሚያተኩርባቸው መስኮች

- ዓለም አቀፍ የሥነምህዳር ሀዉስ /Global Ecology House (GEH)
- የሰነ-ሰው ሀዉስ (Humanities House) (HH)
- ራሳቸውን የቻሉ/በምንም ወይም በትንሽ (የአስተማሪ) ክትትል በግል የሚወሰዱ የትምህርት ፕሮግራሞች (ISP) (Independent Studies Program) (ISP)
- የሳይንስ፣ ሂሳብ፣ የኮምፒውተር ሳይንስ ሃውስ (SMCSH)

## አራት የመማሪያ ሃዉስ ስለሚገኙ—እርስዎ ይወስኑ

በማመልከቻቸው መጣራት ሂደት መሳተፍ ያለባቸው ተማሪዎች ማመልከት የሚችሉት ለ፡- Global Ecology House, Humanities House እና Science, Math, Computer Science House ብቻ ነው። ለሶስቱ ቤቶች ሁሉ ወይም ከሁሉም ለማናቸውም (ሁለት) የተቀናጁ የመማሪያ ቤቶች (ሃውሶች) ሊጋበዙ ይችላሉ። እነኝህ ተማሪዎች አንድ/ነጠላ የመማሪያ ቤት (ሃውስ) መምረጥ አለባቸው። በኮከብ / አስተሪስክ/ምልክት (*) የተሰየሙ/የተለዩ ኮርሶችን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ ተማሪዎች የመማሪያ ቤት በስኬታማነት ያጠናቀቁበት ምስክር ወረቀት (a House Certificate of Achievement) ያገኛሉ።

ሌሎች ሁሉም ተማሪዎች ራሱን ከቻለ የጥናት መርሃ ግብር ጥቅም ያገኛሉ። ልክ የኮሌጅ የመጀመሪያ አመት እና የሁለተኛ አመት ተማሪዎች መሠረታዊ የምረቃ ማሟያቸውን በሚያ ጠናቅቁበት ሁኔታ ተማሪዎች የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመውሰድ ላይ ባሉበት አመት አብዛኛውን የመመረ ቂያ መስፈርቶች ያሟላሉ። ተማሪዎች ኮር ሶችን ለጁኒየር አመት (ለ11ኛ ክፍል) በሚ መርጡበት ጊዜ፣ የISP የስኬት ምስክር ወረቀት ለማግኘት የመማሪያ ቤት ትኩረት የሚመርጡት ጁኒዬሮች (11ኛ ክፍል) እና ሲኒየሮች (12ኛ ክፍል) ሆነው በመረጧ ቸው ኮርሶች መሰረት ነው።



ለበለጠ መረጃ እባክዎን የ MCPS ልዩ ፕሮግራሞች ድረ ገጽ ይጎብኙ ፡-

www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms

ወይም የፑልስቪል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ድረ-ገጽ፡-

www.montgomeryschoolsmd.org/schools/poolesvillehs/magnet/ ይጎብኙ

## የዓለም አቀፍ ሥነምህዳር ሃውስ

### ሳይንስ/ማህበራዊ ጥናቶች/ምርምር/የመስክ ጥናቶች

የዓለም አቀፍ ሥነምህዳር (Global Ecology) ተማሪዎች በጥብቅ የሳይንስ እና የማህበራዊ ጥናቶች ስርአተ-ትምህርቶች ላይ አትኩረው የመሰልጠን (ስፔሻላይዝ የማድረግ) እድል አላቸው። እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ የሚከተሉትን ለማድረግ እድል አለው/ላት፦-

- የአካባቢያዊ ጉዳዮችን ከአንድ በላይ የጥናት መስክ ግንኙነት ባላቸው ጥብቅ የሳይንስና ማህበራዊ ጥናቶች ሥርዓተ ትምህርት አማካይነት የማጥናት እድል ይኖራቸዋል፣
- የመስክ፣ የቤተ-ሙከራ/ላብራቶሪ፣ የሳይንሶች፣ እና የማህበራዊ ጥናቶች የምርምር ክህሎቶችን ማሳደግ፣
- የአካባቢያዊ ዜግነትን ንቃት/ግንዛቤ መኮትኮት ማጎልመስ፣ እና
- የአካባቢያዊ ጥናት ከፍተኛ/ሲኒዬር ፕሮጀክት ማጠናቀቅ።

## የስነ-ሰው (HUMANITIES) መማሪያ ሃውስ

### እንግሊዝኛ/የማህበራዊ ጥናቶች/ምርምር

የስነ-ሰው (Humanities) ተማሪዎች በነጻ/ራስን የቻለ የትምህርት ዕድል/scholarship ላይ ያተኮሩ የሚዲያ ዝግጅቶችን፣ የባህል እና ፖለቲካዊ ጥናቶችን፣ ስነ-ጥበቦች፣ እና ኮሙዩኒኬሽን የማጥናት እድል አላቸው። እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ የሚከተሉትን የማድረግ እድል አለው/አላት፦-

- ሰብአዊ ሥርአተትምህርትን/ከሪኩለምን ፈርጀ ብዙ የትምህርት ዓይነት/ጥናት ጋር በማያያዝ በትክክለኛነት ማካሄድ፣
- የምርምር ክህሎቶችን፣ በጥልቀት የማሰብ እና የማገናዘብ ችሎታዎችን (critical thinking)፣ እና የቃል እና የጽሁፍ መግባባቶችን (ኮሙዩኒኬሽን) ማሳደግ እና ማዳበር/እንዲረቅ/እንዲመጥቅ ማድረግ፣
- የመገናኛ ብዙሃን ውጤቶችን ለማዳበር ከጓደኛሞች ጋር መሥራት፣ እና
- ራስን ችሎ/በግል የሚሰራ የመጨረሻ አመት (senior) የምርምር ፕሮጀክትን ማጠናቀቅ

## ራሳቸውን የቻሉ የትምህርት/ጥናቶች ፕሮግራም

### ሥነህይወት (Biological) እና አካላዊ/የተፈጥሮ (Physical) ሳይንስ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ጥናቶች፣ሙዚቃ፣ አርት፣ የመገናኛ ብዙሃን /ሚዲያ/ ጥናቶች፣ ቴክኖሎጂ እና የሂሳብ ጥናቶች፣ መሰረታዊ/የጅማሮ/Original ጥናቶች

ራሳቸውን የቻሉ የትምህርት/ጥናቶች ፕሮግራም ተማሪዎች የግድ እንዲወስዱ የሚጠየቁ የጥናት መስኮችን በመውሰድ እና የመጨረሻ/የመመረቂያ ፕሮጀክታቸውን በማቅረብ ባተኮሩበት በራሳቸው የጥናት እቅድ የመካን (ስፔሻላይዝ የማድረግ) እድል አላቸው። ራሳቸውን የቻሉ የትምህርት/ጥናቶች ፕሮግራም ተከታታይ እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ የሚከተሉት እድል ይኖረዋል/ራታል —

- በሥራ /ኮሌጅ ላይ ትኩረት ያደረገን ጥብቅ ሥርአተ-ትምህርቶችን የመከታተል፣
- ምርምር፣ ችግርን የመፍታት ክህሎት፣ እና ማሳየት/ማረጋገጫ የመስጠት ምርመራን መፍትሔ ለማግኘት ከጓደኞች ጋር መሥራት፣
- ቀልብ የሚስብ እና የሚማርክ ሙያ/ፕሮፌሽን መፈለግ፣ እና
- Project Lead The Way (PLTW) ተብሎ የሚታወቀውን ጥብቅ የኢንጅነሪንግ ፕሮገራም ማጠናቅቅ

## የሳይንስ፣ የሂሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ መማሪያ ሃውስ

### የላቀ/Advanced/ ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ/ምርምር

የሳይንስ፣ የሂሳብ፣ እና የኮምፕዩተር ሳይንስ ተማሪዎች ችግር በመፍታት ክህሎቶች እና ምርምር ላይ ትኩረት ባደረጉ ጥብቅ የሂሳብ እና የሳይንስ ስርአተ-ትምህርቶች የመካን/ስፔሻላይዝ የማድረግ እድል አላቸው። እያንዳንዱ የሳይንስ፣ የሂሳብ፣ እና ኮምፕዩተር ሳይንስ ተማሪ የሚከተለው እድል ይኖረዋል/ይኖራታል—

- በኢንጅነሪንግ ፕሮብሌም ማቃለል መስፈርቶች ላይ ያተኮረ ጠንካራ የሳይንስ፣ የሂሳብ፣ እና የኮምፒውተር ሳይንስ ሥርአተ ትምህርት/ከሪኩላ መከታተል፣
- በፕሮብሌም መፍታት፣ትንተና፣ እና የላቦራቶሪ/ቤተሙከራ ምርመራዎች ላይ ክህሎቶችን ማሳደግ እና ማጎልበት፣
- የሂሳብ፣ ሳይንስ፣ እና ኢንጂነሪንግ ችግሮችን ለመፍታት ከትምህርት ጓዶቻቸው ጋር የመስራት፣ እና
- ከተማሪው/ዋ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ራሱን የቻለ የሳይንስ ምርምር ፕሮጀክት ማጠናቀቅ።

**ሁሉም የ(MCPS) ኮርስ መግለጫዎች በ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ማስታወቂያ (High School Course Bulletin) ወይም በድረ-ገጽ ላይ mcpscourses.org ይገኛሉ።**

# ዓለም አቀፍ የሥነምህዳር ቤተ-ጥናት/ሃዉስ (Global Ecology House)

**ተማሪዎች ከበርካታ የሥነምህዳር ቤተጥናት/Global Ecology House (GEH) ኮርሶች ይመርጣሉ። ዓለም አቀፍ ስኬት ሠርተፊኬት ለማግኘት ኮከብ (*) ምልክት የተደረገባቸው ኮርሶች በተሟላ ሁኔታ ተጠናቀው መሞላት አለባቸው።**

| | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|
| እንግሊዝኛ | • የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 9 | • የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 10 | • የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 11<br>• AP እንግሊዝኛ ቋንቋ እና ድርሰት/ቅንብር (AP English Language and Composition) | • የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 12<br>• AP እንግሊዝኛ ስነ-ጽሑፍ |
| ☗ ማህበራዊ ጥናቶች | • ግሎባል የላቀ የዩ.ኤስ ታሪክ/Global Honors US History* | • ዓለም አቀፍ AP ብሔራዊ፣ ስቴት እና አካባቢ አስተዳደር/መንግስት* (Global AP National State and Local Government)* | • ዓለም አቀፍ AP የዓለም ታሪክ* (Global AP World History)* | |
| ☗ ሳይንስ | • ግሎባል የላቀ ባዮሎጂ/Global Honors Biology* | • ግሎባል የላቀ ኬሚስትሪ/Global Honors Chemistry* | • ግሎባል የላቀ ፊዚክስ/Global Honors Physics (H)* ወይም AP ፊዚክስ 1 እና 2/ AP Physics 1 & 2 | • ዓለም አቀፍ AP የአካባቢያዊ ሳይንስ* Global AP Environmental Science* |
| ☗ ቤተ-ጥናት ትኩረት HOUSE FOCUS | • AP የኮምፒውተር ሳይንስ መርሆዎች/ፕሪንስፕልስ* | • ተማሪዎች በጠቅላላው የ6 ሴሚስተሮችን ተጨማሪ በምርጫ የሚወሰዱ የግሎባል ኮርሶችን** በሁለተኛ ዓመት ተማሪነታቸው ጊዜ፣ ጁንየር፣ እና/ወይም ሲንየር ዓመታቸው ላይ ማጠናቀቅ አለባቸው። | | |
| ሂሳብ | • የላቀ ጂኦሜትሪ/Honors Geometry<br>• የላቀ አልጄብራ 2/Honors Algebra 2 | • የላቀ ፕሪካልኩለስ/Honors Precalculus<br>• የላቀ አልጀብራ 2/Honors Algebra 2 | • የላቀ ፕሪካልኩለስ/Honors Precalculus<br>• AP ካልኩለስ BC፣ AP/AP Calculus BC፣ AP<br>• ካልኩለስ AB/Calculus AB<br>• AP አኃዛዊ መረጃ/ስታቲስቲክስ<br>• ካልኩለስ ከመተግበሪያዎች ጋር/Calculus with Applications | • ካልኩለስ ከመተግበሪያዎች ጋር (Calculus with Applications)<br>• AP ካልኩለስ AB/AP Calculus AB<br>• AP ካልኩለስ BC/AP Calculus BC<br>• Ap አኃዛዊ መረጃ/ስታቲስቲክስ<br>• መድብለ ተለዋዋጭ ካልኩለስ (Multivariable Calculus) |
| የሚመረጡ | • ስለ ምህንድስና ንድፍ መግቢያ A/B (Project Lead The Way)<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) | • ስለ ምህንድስና መርኾ/ፕሪንስፕሎች Principles of Engineering (Project Lead The Way)<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ — ስፓንሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ኪነ-ጥበባት | • የሲቪል ምህንድስና እና ንድፍ (Project Lead The Way)<br>• ዲጂታል ኤሌክትሮኒክስ (PLTW<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) | • ምህንድስና ንድፍ እና እድገቱ/ዴቨሎፕመንት (Project Lead The Way)<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) |

☗ ኮርሶች ተያያዥነት ለኖራቸውና ቀስ በቀስ ሊመደቡ ይችላሉ።

* ለዓለምአቀፍ-ክንውን/ግሎባል የምስክር ወረቀት ኮርስ ያስፈልጋል

** AP Science and Social Studies courses and Marine Biology, Cellular Physiology, Optics, Organic Chemistry, Thermodynamics, Quantum Physics, Analytical Chemistry, Biochemistry, Intro. to Physical Chemistry, Intro to Genetic Analysis, PLTW courses, Research Design, Research Project A, Internship (max. 2 semester credits), Materials Science, Robotics, Linear Algebra, Discrete Math, Computer Graphics, Software Design, Networking, Writing Mobile Applications, Intro to Cyber Forensics/Security, Programming Languages

# ስነሰዉ ቤተ-ትምህርት/ሃዉስ

ተማሪዎች ከስነሰዉ ቤተ-ትምህርቶች ውስጥ የሚፈልጓቸውን ለመምረጥ ይችላሉ (HH)። የስነሰዉ ጥናት ሰኬት ሠርተፊኬት ለማግኘት የኮከብ (*) ምልክት የተደረገባቸውን ትምህርቶች/ኮርሶች በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቅ አለባቸው።

| | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|
| ⌂ እንግሊዝኛ | ስነ-ሰው የላቀ እንግሊዝኛ 9*/Humanities Honors English 9 | ስነ-ሰው የላቀ እንግሊዝኛ*/Humanities Honors English 10 | ስነ-ሰው AP እንግሊዝኛ ቋንቋ እና ድርሰት/AP English Language and Composition* | AP እንግሊዝኛ ስነ-ጽሑፍ* |
| ⌂ ማህበራዊ ጥናቶች | ስነ-ሰው (Humanities)<br>AP NSL አስተዳደር/AP NSL Government* | AP ዩ.ኤስ ታሪክ/AP US History* | ስነ-ሰብ AP የዓለም ታሪክ* | |
| ⌂ ቤተ-ጥናት ትኩረት | ስነ-ሰብ ትችት/አቃቂር/ሃያሲ-ጥናት A/B*<br>(Criticism in the Humanities A/B*) | • AP ትምህርታዊ ጉባኤ/ሴሚናር* | AP ስነ-ጥበብ ታሪክ*<br>ተማሪዎች ከመረጧቸው Humanities electives** በጁንየር እና/ወይም በሲንየር ዓመታቸው በጠቅላላ 4 ሴሚስተሮችን ማጠናቀቅ አለባቸው። | AP ጥናት/ምርምር * |
| ሳይንስ | የላቀ ባዮሎጂ/Honors Biology | • የላቀ ኬሚስትሪ/Honors Chemistry | • የላቀ ፊዚክስ/Honors Physics | |
| ሂሳብ | • የላቀ ጂኦሜትሪ/Honors Geometry<br>• የላቀ አልጀብራ 2/Honors Algebra 2 | • የላቀ ፕሪካልኩለስ/Honors Precalculus<br>• የላቀ አልጀብራ 2/Honors Algebra 2 | • AP ካልኩለስ BC, AP ካልኩለስ AB<br>• AP አኃዛዊ መረጃ/ስታቲስቲክስ<br>• ካልኩለስ ከአፕስ /መተግበሪያዎች ጋር/ Calculus with Applications<br>• የላቀ ፕሪካልኩለስ/Honors Precalculus | • መድብለ ተለዋዋጭ (Multivariable) ካልኩለስ<br>• AP ካልኩለስ BC, AP ካልኩለስ AB<br>• AP አኃዛዊ መረጃ/ስታቲስቲክስ<br>• ካልኩለስ ከአፕስ/ከመተግበሪያዎች ጋር/ Calculus with Applications |
| በምርጫ የሚሰጡ ትምህርቶች/ኮርሶች | • የምህንድስና ንድፍ መግቢያ<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ)<br>• AP የኮምፒውተር ሳይንስ መርሆዎች/ፕሪንስፕልስ | • የምህንድስና መርህ/ስረ መሠረት/Principles of Engineering (PLTW)<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) | • ዲጂታል ኤሌክትሮኒክስ (PLTW<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ)<br>• ሲቪል ምንህንድስና እና የንድፍ ጥበብ/Civil Engineering & Architecture (PLTW) | • ምህንድስና ንድፍ እና እድገት<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) |

⌂ ኮርሶች ተያያዥነት ለኖራቸውና ቀስ በቀስ ሊመድቡ ይችላሉ።

* ስነ-ሰብ ጥናት የ ሰኬት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ኮርስ መውሰድ አስፈላጊ ነው

** የ AP ኮርሶች በሥነ ጥበብ/Art፣ ሙዚቃ/Music፣ ማህበራዊ ጥናት/Social Studies ወይም የዓለም ቋንቋዎች እና ሙግት/World Languages and Debate፣ ጋዜጠኝነት/Journalism፣ ዓመታዊ መጽሔፍ/Yearbook፣ ቲአትር/Theater፣ የፈጠራ ስነጽሑፍ/Creative Writing፣ ፊልም እንደሥነጽሑፍ/Film as Literature።

ተጨማሪ በምርጫ የሚሰጡ ትምህርቶች

የባሕር ህዋሳዊ ጥናት/ማሪን ባዮሎጂ (Marine Biology)፣ ህዋሳዊ ፊዚዮሎጂ (Cellular Physiology)፣ እይታ (Optics)፣ ኦርጋኒክ ኬሚስትሪ (Organic Chemistry)፣ ቴርሞዲያነምክስ(Thermodynamics)፣ ኳንተም ፊዚክስ (Quantum Physics)፣ ኬሚስትሪ-ትንታኔ (Analytical Chemistry)፣ ባዮኬሚስትሪ (Biochemistry)፣ ፊዚካል-ኬሚስትሪ መግቢያ (Intro. to Physical Chemistry)፣ ሥርወ-ዝርያ/ጄኔቲክ ትንታኔ መግቢያ (Intro to Genetic Analysis)፣ PLTW ትምህርቶች፣ የዲዛይን ምርምር/ጥናት Research Design፣ ምርምር/ጥናት ፕሮጀክት A Research Project A፣ ተሞክሮ-ሥራ/ኢንተርንሺፕ ቢያንስ 2 ሴምስተር-ክሬዲት Internship (max. 2 semester credits)፣ ቁሳዊ-ሳይንስ Materials Science፣ ሮቦቲክስ Robotics፣ ሊንየር አልጀብራ Linear Algebra፣ ዲስክሪት ማትስ Discrete Math፣ ኮምፒውተር-ንድፍ Computer Graphics፣ ሶፍትዌር-ንድፍ Software Design፣ አውታረመረብ Networking፣ ሞባይል አፕስ/መተግበሪያ መጻፍ/ Writing Mobile Applications፣ ስለ ሳይበር ፎረንዚክስ መከላከል መግቢያ ትምህርት Intro to Cyber Forensics/Security፣ የፕሮግራሚንግ ቋንቋዎች Programming Languages

# ለ ግለ-ጥናት ፕሮግራም ሠርተፊኬት ተፈላጊ/መወሰድ ያለባቸው

የመጀመርያ እና ሁለተኛ ዓመት ላይ መጠቅ-ትምህርት (honors) ወይም AP ያላቸውን ትምህርቶች እንዲወስዱ ይበረታታሉ። በትምህርት መስክ ጉዞዎች ውስጥ በመሳተፍ ኮሌጅ የመግባት እና ወደ ስራ የመሠማራት መንገድ የመዳሰስና ከክፍል ውጭ የመማር ልምድ ለመቅሰም እድሎች ይኖራቸዋል። የሶፈሞር ዓመት/10ኛ ክፍል ማለቂያ ላይ ከአማካሪዎቻቸው ጋር ሲገናኙ ተማሪዎቹ ወደ ፊት ለማጥናት/ለመማር ስለሚያቅዱት ዓይነት ትምህርት ከ ISP አንዱን መወሰን ይኖርባቸዋል የሚያተኩሩበት ዝንባሌ በመካከለኛ እና በከፍተኛው ዓመት የሚጠናቀቅ ነዉ።

| የትኩረት/ዝንባሌ አቅጣጫ | ተፈላጊዎቹ*-4.0 ነጥብ ክሬዲት ከሚከተሉት ትምህርቶች/ኮርሶች** |
|---|---|
| ስነዮታዊ/የባዮሎጂ እና የተፈጥሮአዊ ሳይንስ (BAPS) | AP ኬሚስትሪ/AP Chemistry፣ AP ፊዚክስ/AP Physics፣ የከባቢ ሳይንስ/Environmental Science፣ AP ከባቢ ሳይንስ/AP Environmental Science፣ AP ባዮሎጂ/AP Biology፣ አናቶሚ እና ፊዚኦሎጂ/Anatomy and Physiology፣ ምድራዊ ሳይንስ/Earth Science፣ ፎረንዚክ ሳይንስ/Forensic Science፣ ሴሉላር ፊዚኦሎጂ/Cellular Physiology፣ ጀኔቲክስ/ Genetics፣ ማሪን ባዮሎጂ/Marine Biology፣ አናሊቲካል ኬሚስትሪ/Analytical Chemistry፣ ዋይልድላይፍ ባዮሎጂ/Wildlife Biology፣ ኦርጋኒክ ኬሚስትሪ/Organic Chemistry፣ ኢንተርንሽፕ Internship |
| ባህላዊ ዐውድ እና የፖለቲካ ትምህርት/ጥናት (CAPS) | AP የዓለም ታሪክ/AP World History፣ AP ስነ-ሰው ጂኦግራፊ/AP Human Geography፣ AP ምጣኔ ሃብት/AP Economics፣ AP ስነጽሑፍ/AP Literature፣ AP ቋንቋ እና ድርሰት/AP Language & Composition, AP NSL አስተዳደር-መንግስት/AP NSL Government፣ AP ኮምፓራቲቭ የመንግስት አስተዳደር፣ ኮምፓራቲቭ ሃይማኖት/AP Comparative Government, Comparative Religion፣ AP የሥነ ጥበብ ታሪክ/AP Art History፣ AP ሳይኮሎጂ/AP Psychology፣ ሳይኮሎጂ/Psychology፣ የጥንታዊ እና የመካከለኛ ዘመን ታሪክ/Ancient and Medieval History፣ የማህበረሰብ ጥናት/ሶስዮሎጂ Sociology፣ ፍልስፍና/ፊሎሶፊ/Philosophy፣ ሕግ/Law፣ ሙግት/ክርክር/Debate፣ የውጭ ቋንቋ (ደረጃ 3 ወይም ከዚያ በላይ)/Foreign Language (level 3 or above)፣ ኢንተርንሽፕ/ Internship |
| ስለ ሙዚቃ/አርት/መገናኛ ብዙኃን ትምህርት (MAMS) | ባንድ/Band፣ ኦርኬስትራ/Orchestra፣ አዝማች/Chorus፣ ጊታር/Guitar፣ ጃዝ ኢንሰምብል/Jazz Ensemble፣ ጋዜጠኝነት/Journalism፣ ቲአትር/Theater፣ ቲቪ ፕሮዳክሽን/TV Productio፣ ፎተግራፍ/Photography፣ ሴራሚክስ/Ceramics፣ የቀለም ቅብ/Painting፣ AP የሥነ ጥበብ ታሪክ/AP Art History፣ ስቱድዮ ሥነ ጥበብ/Studio Art፣ AP የስቱዲዮ ሥነ ጥበብ/AP Studio Art፣ የፈጠራ ስነጽሑፍ/Creative Writing፣ የዓመቱ መጽሐፍ/Yearbook፣ የሚድያ ትምህርት/Media Literacy፣ ሙግት/ክርክር/Debate፣ ስነጽሑፍ እንደ ፊልም/Literature as Film፣ የድረ-ገጽ ንድፍ/Web Design፣ ኢንተርንሽፕ/Internship |
| መንገድ ጠቋሚ ፕሮጀክት (Project Lead The Way (PLTW) | ስለ ምህንድስና መግቢያ/Introduction to Engineering (IED)፣ የምህንድስና መርሆች/ስርወመሠረት/Principles of Engineering (POE)፣ ዲጅታል ኤሌክትሮኒክስ/Digital Electronics (DE)፣ ሲቪል ምህንድስና እና ንድፍ/Civil Engineering and Architecture (CEA)፣ የንድፍ ምህንድስና እድገት/Engineering Design and Development (ED) |
| የቴክኖሎጂ እና የሂሳብ ትምህርቶች (TAMS) | ኔትዎርኪንግ/Networking፣ ኮምፒውተር ግራፊክስ/Computer Graphics፣ AP ኮምፒውተር ሳይንስ/AP Computer Science፣ የአልጎሪዝም ትንታኔ/Analysis of Algorithms፣ ማቴሪያላዊ ሳይንስ/Materials Science፣ ስታትስቲክስ/Statistics፣ AP ስታቲስቲክስ/AP Statistics፣ AP ካልኩለስ AB & BC/AP Calculus AB & BC፣ መድብለ ተለዋዋጭ ካልኩለስ/Multivariable Calculus፣ ማቴሪያላዊ ሳይንስ/Materials Science፣ ሮቦቲክስ/Robotics፣ AP የኮምፒውተር ሳይንስ መርሆች/ስረመሠረት/AP Computer Science Principles፣ ኢንተርንሺፕ/Internship |
| የመጀመሪያው ጥናት | በመረጥከው/በመረጥሽው ሥራ የሚፈለገውን አራት ነጥብ/ 4.0 credits required † ለመገንባት ከካውንስለር ወይም ከማኔት አስተባባሪ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል † |

* ሁሉም የትምህርት ዓይነት በየዓመቱ የሚሰጥ አይሆንም አዳዲስ ኮርሶችም እንዲሁ ሊጨመሩ ይችላሉ።

** ኮርሶቹ መጠናቀቅ ያለባቸው በጁንየር እና በሲንየር ዓመት ነው።

† በ PHS የሚሰጡ ፕሮግራሞችን ጨምሮ MCPS የሚሰጡ እንደ:- ቶማስ ኤድሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እሳት አደጋ EMT አካዳሚ/ Fire/EMT Academy፣ AP ለቃ-ጥናት/AP/Honors Course፣ ተሞክሮ-ስራ/internships ወይም በኮሌጅ የስራ/ሙያ ጥናት እና እድገት

# ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ የተራዘመ/ተቀጣይ ሠዓት ትምህርት

SMCSH ሁለት የተለያዩ በይነገጽ/ፕሮግራም ምስክር ወረቀቶች ይኖሩታል። የላቀ ሚሆነው "በምርምር ችሎታ/ከፍተኛ ብቃት" የሚሰጠው ምስክር ወረቀት/ሰርተፊኬት ነው። ቀጣዩ አማራጭ የምርምር ተጓዳኝነት የሌለው/የማያስፈልገው ምስክር ወረቀት/ሠርተፊኬት ይሆናል። ተማሪዎች ከሁለት አንዱን SMCSH ምስክር ወረቀት/ሠርተፊኬት ለማግኘት ቢያንስ BC ካልኩለስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል።

| | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|
| እንግሊዝኛ | • የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 9 | • የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 10 | • AP ቋንቋ እና ድርሰት/ቅንብር<br>• የላቀ እንግሊዝኛ/Honors English 11 | • AP እንግሊዝኛ ስነ-ጽሑፍ |
| ⌂ ማህበራዊ ጥናት/ማህበራዊ ሳይንስ | • የላቀ የዩ.ኤስ ታሪክ/Honors US History | • AP ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ መስተዳድር/መንግስት<br>• የላቀ ብሔራዊ የስቴት እና የአካባቢ መንግስት(አስተዳደር)/Honors National State & Local Government | • AP የዓለም ዝክረ-ታሪክ<br>• የላቀ ዘመናዊ የዓለም ታሪክ | |
| ⌂ ሳይንስ | • መጠቅ ሳይንስ 1-ፊዚክስ* (Advanced Science 1—Physics*)<br>• መጠቅ ሳይንስ 2-ኬሚስትሪ* | • መጠቅ ሳይንስ 3-ምድረሳይንስ* Advanced Science 3—Earth Science*<br>• መጠቅ ሳይንስ 4-ባዮሎጂ* | • ተማሪዎች በመለስተኛ እና በመጨረሻ ትም/ዓመታቸው 6 ሴሚስተር በምርጫ የሚወስዷቸው SMCS electives** ማጠናቀቅ አለባቸው። | |
| ⌂ ጥናት/ምርምር | • ውስብስብ-ችግርን ለመፍታት ጥናትና-ምርምር እንዲሁም ሙከራዎች 1 A/B* | • SMCS የምህንድስና መርሆች/ስረመሠረቶች/ SMCS Principles of Engineering* | • የንድፍ ምርምር/Research Design* እና<br>• የምርምር/ጥናት ፕሮጀክት A* | • የምርምር/ጥናት ፕሮጀክት B |
| ⌂ የኮምፒውተር ሳይንስ | • መሠረታዊ የኮምፒውተር ሳይንስ A/B* | • የቀመር ስልቶች/Algorithms እና የውህብ/ Data/ መረጃ መዋቅር /(Data) A/B* | | |
| ሂሳብ | • ማግኔት ጆሜትሪ*<br>• ማግኔት ቅድመ-ካልኩለስA/B* ወይም<br>• ማግኔት ቅንተዛምዶ/ፈንክሽንስ A/B* (Magnet Functions A/B)* | • ማግኔት ቅድመ-ካልኩለስ A/B<br>• ማግኔት ቅድመ-ካልኩለስ C/D<br>• ትንተና 1 A/B ወይም AP ካልኩለስ BC | • ማግኔት ቅድመ-ካልኩለስ C/D<br>• ትንተና 1 A/B ወይም AP BC ካልኩለስ (Analysis 1 A/B or AP BC Calculus)<br>• ቀስት መስመር ካልኩለስ A/B ወይም መድብለ ተለዋዋጭ ካልኩለስ A/B (Vector Calculus A/B or Multivariable Calculus A/B)<br>• AP ስታቲስቲክስ ወይም አፕላይድ ስታቲስቲክስ/ሊንየር አልጀብራ/AP Statistics* or Applied Statistics*/Linear Algebra | • ትንተና 1 A/B ወይም AP ካልኩለስ BC (Analysis 1 A/B or AP Calculus BC)<br>• ቀስት መስመር ካልኩለስ A/B ወይም መድብለ ተለዋዋጭ ካልኩለስ A/B Vector Calculus A/B or Multivariable Calculus A/B<br>• ሊኒየር አልጀብራ<br>• ዲስክሪት ማትስ (ሂሳብ) |
| በምርጫ የሚሰጡ ትምህቶች | • የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) | • የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) | • የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ) | • የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>• የውጭ ቋንቋ-ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ<br>• ሥነ-ጥበብ (ፋይን አርትስ)<br>• ተሞክሮ-ሥራ (Internship) |

⌂ • ትምህርቶቹ ተያያዥነት ያላቸውና በቅደምተከተል የሚሰጡ ይሆናሉ።

* • የ SMCS ስኬት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ኮርስ መውሰድ ያስፈልጋል

** • የምርምር ፕሮጀክት/Research Project B፣ ሴሉላር ፊዚኦሎጂ/Cellular Physiology፣ ኦፕቲክስ/Optics፣ ኦርጋኒክ ኬሚስትሪ/Organic Chemistry፣ ቴርሞዳይናሚክስ/Thermodynamics፣ ኳንተም ፊዚክስ/Quantum Physics፣ አናሊቲካል ኬሚስትሪ/Analytical Chemistry፣ ባዮኬምስቲ/Biochemistry፣ የፊዚካል ኬሚስትሪ መግቢይ/Intro. to Physical Chemistry፣ የጀንቲክ አናሊሥስ መግቢያ/Intro. to Genetic Analysis፣ ማሪን ባዮሎጂ/Marine Biology፣ AP ኬሚስትሪ/AP Chemistry፣ AP ባዮሎጂ/AP Biology፣ AP ፊዚክስ B ወይም C/AP Physics B or C፣ የአልጎሪዝም ትንታኔ/Analysis of Algorithms፣ የኮምፒውተር ግራፊክስ/Computer Graphics፣ የሶፍትዌር ንድፍ/Software Design፣ ኔትዎርኪንግ/Networking፣ ሮቦቲክስ/Robotics፣ ቁሳዊ/ማቴሪያላዊ ሳይንስ/Materials Science፣ የሞባይል አፕሊኬሽን ጽሑፍ/Writing Mobile Applications፣ የሳይበር ፎረንዚክስ/ደህንነት/Intro to Cyber Forensics/Security፣ የፕሮግራም ቋንቋዎች/Programming languages

# የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ
# MCPS Nondiscrimination Statement

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሔር ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የስደተኝነት ሁኔታ፣ ጾታ፣ ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግንኙነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች የኑሮ ደረጃ/አቋም/ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት፣ እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ሁኔታዎችን ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገ ሕገ-ወጥ አድሎ/መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ በሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነትን፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ፣ ሲደረግ የቆየ ትጋትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፡-ጥላቻ፣ ሁከት፣ ደንታቢስነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ንቀት፣ ወይም ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደምብ/Policy ACA ስለ ጸረ-መድሎ፣ ፍትህ፣ የዳበረ ባህል ይመርምሩ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ/ተፈላጊ መሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች የሚረጋገጡት በምንም ዓይነት ግለሰብ ባለበት(ባለባት) ምክንያት ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በቅድሚያ መወሰድ ስላለባቸው የፍትህ እርምጃዎች የተዛባ አመለካከትን፣ ማረጋገጫ የሌላቸው የማዳላት/ልዩነት አፈጻጸሞችን የሚያስከትሉትን አሉታዊነት፣ የትምህርት እና የሥራ መቀጠር እኩልነትን የሚያሰናክሉ መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ አሠራር ደንቃራዎችን በተለይ ያስገነዝባል።

| በMCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በMCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና የክትትል/የምርመራ መምሪያ<br>Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት የአፈጻጸም ክፍል<br>Office of School Administration Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2540<br>COS-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

* ክትትል፣ ቅሬታ/ስሞታ፣ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፤ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፣ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 240-740-3230 ሊቀርብ/ሊመራ ይችላል። ለሰራተኞች መገልገያዎች ወይም ማሻሻያዎች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations/ የሰራተኛ ተሳትፎ እና የስራ ግንኙነት የአፈጻጸም እና የክትትል (የምርመራዎች) መምርያ፣ ስልክ፡- 240-740-2888 ሊመሩ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ አድሎአዊነት ቅሬታዎች ለሌሎች ኤጀንሲዎችም ፋይል ሊደረጉ ይቻላል። እነርሱም፡- the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg, 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); ወይም U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህ ሠነድ ካስፈለገ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎችና በሌላ አማራጭ ቅርፀት ሊገኝ ይችላል። በአካል ጉዳተኝነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የህዝብ ኢንፎርሜሽን እና የድረ-ገጽ አገልግሎት ክፍልን በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837, 1-800-735-2258 (ሜሪላንድ ማዞሪያ), ወይም PIO@mcpsmd.org. የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም የንግግር ትርጉም/ምልክት አገልግሎት ለማግኘት የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።


MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

በመገልገያ እቃዎች/ቁሳቁሶች አስተዳደር መምሪያ ለኮንሶርሺያ ን/ክፍል
የዝንባሌ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ታተመ
Department of Materials Management for the Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS)
ትርጉም፡- Language Assistance Services Unit • Department of Communications
0018.19ct • Editorial ፣ Graphics & Publishing Services • 8/18 •2K

PRODUCED BY LOCAL 500 SEIU MEMBERS